# ጽዮን ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን
**ኒውዮርክ**

# St. Mary of Zion
**Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**
**New York**

October 26, 2020

የተከበራችሁና የተወደዳችሁ የድዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባሎችና የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች፤

እንኳን ለተቀደሰው የድዮን ቅድስት ማርያም ዓመታዊ ክብረ በዓል በሰላምና በጤና ጠብቆ አደረሳችሁ።

ሁላችሁም እንደምታውቁት አለማችንን በአጋጠማት የወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ቤተክርስቲያናችን ምናባዊ (virtual)የመንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎት ከማርች 22 ቀን 2020 (March 22, 2020) ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በማበርከት ላይ ትገኛለች።

የኮቪድ 19 (covid-19) ወረርሽኝ በሽታ በጣም አስከፊና ብዙ ሰዎችን ለከፍተኛ ህመምና ሕይወት መጥፋት የዳረገ መሆኑን ቤተክርስቲያናችን በፍጥነት ተገንዝባ፣ በሰበካ ጉባኤ አስተዳደር የጤና ኮሚቴ አማካይነት ባለማቋረጥ በየእሁዱ ኮቪድ 19ኙን በተመለከተ ትምህርትና ማሳሰቢያ በመስጠት ግዴታዋን እየተወጣች ነው። በመሆኑም የጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አባሎችና የፕሮግራሙ ተከታታዮች ከዚህ በየሳምንቱ ከሚሰጠው ትምህርትና ማሳሰቢያ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።ይህንን ወረርሽን በሽታ ለማሸነፍና ከዓለም ላይ ለማጥፋት የምንችለው በየቤታችን ሆነን እግዚአብሕርን በፀሎታችን በመማፀን፣ በመለመንና እራሳችንን ከበሽታው ለመጠበቅ የተማርናቸውን ትምህርቶችና ማሳሰቢያዎች በሥራ ላይ በማዋል ነው።

ውድ የጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተሰቦች፤

ቤተክርስቲያናችን የኒውዮርክ ህግ በሚፈቅደው መሠረት በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመክፈት ማንኛውንም ጥረት እያደረገች ነው። ይህንንም በተመለከተ የንብረትና የጥገና ክፍላችን አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በመግጠምና የቤተክርስቲያኑን ያጠቃቀም ፕላን በማውጣት ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

በመጨረሻም በየዓመቱ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም የምናደርገው ስጦታ እንዳይጓደልና በረከቷን ለማግኘት አቅም በፈቀደ እራሳችሁን ሳታስጨንቁ የምትችሉትን ሥጦታ እንድታበረክቱ በትህትና እያሳሰብን ከዚህ ደብዳቤ ጋር የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ካርድና (pledge card) የተከፈለ ፓስታ (postage paid envelope) አያይዘን ልከናል።

የእግዚአብሔር ሰላምና ፍቅር ከሁላችሁ ጋር ይሁን
እግዚአብሔር በጤና ጠብቆ በዓይነ ሥጋ ለመገናኘት ያብቃን

መላከ ገነት ገዛኸኝ ገ/ክርስቶስ
የጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ

**77 High Street Yonkers, NY 10703 (914) 338-7514 [www.stmaryofzion.org](http://www.stmaryofzion.org) StMaryNY@gmail.com**

# በኒዉዮርክ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እርዳታ ማሰባሰቢያ ቅጽ

---

## St.Mary of Zion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church of New York Pledge Form

"በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠዉን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ ያሰበዉን ይስጥ በሐዘን ወይም በግድ አይደለምና።" ፪ኛ ቆሮ፱፥፮-፯

ለሰጡት ሁሉ እግዚአብሔር በእጥፍ ይስጥዎ!!

"The Person who sows sparingly will also reap sparingly, and the Person who sows generously will also reap generously. Each one of you should give just as he has decided in his heart, not reluctantly or under compulsion, Because God loves a cheerful giver" 2 Corinthians 9:6

ስም (Name) ______________________________ ስልክ (Phone) ____________________

ኢ-ሜል (E-Mail) ______________________________________

ቃል የገቡት የገንዘብ ልክ $ ____________ (Total Pledged) በዛሬዉ ቀን የከፈሉት $ ____________ (Paid Today) ቀሪ $____________ (Remaining)

Mailing Address: 77 High Street Yonkers, NY 10703 Tel: (914) 338 7514
Tax ID # 13-3807181 Please Make checks Payable to: St. Mary of Zion Ethiopian Orthodox Church